| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |

ኃይሌ አሰግዴ
የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስትር

የባህር መዝገብ
ገጽ ______

# የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች የሠሌዳ ቁጥር መመዝገቢያ መዝገብ

| ተ.ቁ. | የሠሌዳ ቁጥር | የኮንስትራክሽን መሣሪያው ዘርፍ | የባለንብረቱ/የድርጅቱ ስም | የሞተር ቁጥር | የሻሲ/የሴሪያል/ ቁጥር | የሠሌዳ ከፍያ ደረሰኝ ቁጥር | የተሰጠበት ቀን | የተረካቢ ፊርማ | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |

ሐምሌ 16 ቀን 1996 ዓ.ም.

# የ ው ስ ጥ   ማ ስ ታ ወ ሻ

ለ ⇨ ክቡር የኮንስትራክሽንና ፐብሊክ ዩቲሊትስ ማኔጅመንት ዘርፍ ሚ/ር ዲኤታ

ከ ⇨ ከዲዛይንና ኮንስትራክሽን ቁጥጥር ፀ/ቤት

ጉዳዩ ⇨ ተጨማሪ የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ምዝገባና ዳይሬክ ምርመራ ለማድረግ የቀረበ መመሪያ እንዲፀድቅልን ስለመጠየቅ፤

በመ/ቤታችን የሚመዘገቡ የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች አመዘጋገብ ሚያዝያ 1993 በወጣው መመሪያ መሠረት መሆኑ ይታወሣል። በዚህ መመሪያ ያልተካተቱ የግንባታ መሣሪያዎች በአገልግሎት ፈላጊዎች በቀረበው ጥያቄ መሠረት ለመመዝገብ አሠራሩ መመሪያን የተከተለ እንዲሆን የቀረበውን ረቂቅ ጥናት እንዲሠራበት እንዲፀድቅልን በትህትና እንጠይቃለን።

ከማክበር ከሠላምታ ጋር

አባሪ፡ 1 ጥራዝ

(1) ለኮንስትራክሽን ዘርፍ
ዶ/ሩት.
የፀደቀ አሠራር ነው
ካቁ ቀርቧል

(2) ለኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ቡ.
· መመሪያው እዚፀደቀ በሥራ ላይ ይዋል።
- በተጨማሪነት የተጠቀሱትን የመሣሪያ ዝርዝር መሰረት ከተገለጸው ሰንጠረዥ፡ በማስታወቂያ ህዝቡ፡ ይገለጽ
20/11/96

በመሠረተ ልማት ሚኒስቴር
የዲዛይን ኮንስትራክሽን ቁጥጥር ጽ/ቤት

# ለምዝገባ ለሚቀርቡ ተጨማሪ የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች የቀረበ ረቂቅ ጥናት

ሐምሌ 1996 ዓ.ም.

# ማውጫ


መግቢያ ........................................................................ 1

1 የጥናቱ ዓላማ ........................................................................ 2

2 የጥናቱ አጠናን ዘዴ ........................................................................ 2

3 በጥናቱ እንዲካተቱ የተደረጉ መሣሪያዎች ........................................ 2

4 ስለመሣሪያዎች አመዘጋገብ የተደረገ ማጣራት ........................................ 2

5 ስለመሣሪያዎች የቴክኒክ ዝርዝርና ዓይነት መረጃዎችን ማሰባሰብ ....... 3

6 የብቃት ምርመራ አገልግሎት ክፍያ ........................................ 3

7 የመሣሪያዎች የቴክኒክ ብቃት ምርመራ አሠራር ዘዴ ........................ 5

8 አባሪዎች፣

1 የአገልግሎት ክፍያ ሰሌት
2 የመሣሪያ የኪራይ ተመን ሰሌት
3 የመሣሪያዎች የገበያ ተፈላጊነት ነጥብ አሰጣጥ
4 የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች የአገልግሎት ክፍያ ለመተመን የወጣ ቀመር

# መግቢያ

መንግሥት የግል ዘርፉን ለማበረታታት ካወጣቸው አዋጆች ውስጥ የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ምዝገባና ቁጥጥር አዋጅ 177/91 የሚጠቀስ ነው፡፡ በዚህ አዋጅ መሠረት የኮንስትራክሽን መሣሪየ ባለንብረቶች መሣሪያዎቻቸውን በማስመዝገብ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ለመውሰድ ለዋስትና መያዣነት አገልግሎት እየተጠቀሙበት ይገኛሉ፡፡

የአዋጁ ተጠቃሚ የሆኑት አዋጁን ተከትሎ በወጣው መመሪያ ውስጥ ዝርዝራቸው የተካተቱት የኮንስትራክሽን መሣሪያ ባለንብረቶች ሲሆኑ ከዚህ ውጭ የሆኑ መሣሪያ ያሏቸው ባለንብረቶች የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ለመሆን ጥያቄ በማቅረብ ላይ ናቸው፡፡ በዚህም መሠረት የባለንብረቶችን ጥያቄ መነሻ በማድረግ በዚህ ጥናት ውስጥ የተካተቱት የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች መመዝገብ እንዲችሉ ለማድረግ ይህ ጥናት ቀርቧል፡፡

## 1. የጥናቱ ዓላማ፣

የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች የባለቤትነት መታወቂያ ደብተርና ሠሌዳ አሠጣጥ በሚ/ር መ/ቤቱ የወጣውን መመሪያ ተከትሎ የሚከናወን ስለሆነ በዚህ ጥናት የተካተቱት የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ዝርዝር የመመሪያው አካል እንዲሆኑ ለማድረግና, አፈጻጸሙ ሥርዓት የተከተለ እንዲሆን ለማድረግ ነው::

## 2. የጥናቱ አጠናን ዘዴ፤

- በአገልግሎቱ ፈላጊዎች የቀረቡትን ጥየቄዎች መነሻ በማድረግ በጥናቱ መካተት ያለባቸው መሣሪያዎች መለየት፣
- በጥናቱ የተካተቱ መሣሪያዎች በሌሎች የመንግሥት አካላት የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ይሰጣቸው እንደሆነ ማጣራት፣
- ስለመሣሪያዎቹ አይነትና የቴክኒክ ዝርዝር መረጃዎችን በመሰብሰብና መሣሪያዎችን በማየት አጠቃላይ ግንዛቤ መውሰድ፣
- በመሣሪያዎች የቴክኒክ ብቃት ምርመራ አደራረግ ወቅት የሚኖሩ የአገልግሎት ክፍያዎችን ቀደም ሲል በወጣው መመሪያ መሠረት መተመን፣

## 3. በጥናቱ እንዲካተቱ የተደረጉ መሣሪያዎች፣

ከአገልግሎት ፈላጊዎች በቀረበው ጥያቄ መሠረት የመቆፈሪያና(Drilling Rigs) የጠጠር መበተኛ (Chip Spreader) መሣሪያዎች በጥናቱ ተካተዋል::

## 4. ስለ መሣሪያዎቹ አመዘጋገብ የተደረገ ማጣራት፣

የጉድጓድ መቆፈሪያ መሣሪያ ባለንብረቶች የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ይሰጣቸው እንደሆነ ለማወቅ በተደረገ ማጣራት ተጠይቀው በተሽከርካሪዎች ላይ ተገጥመው ለሚሰሩት በመንገድ ትራንስፖርት ባለሥልጣን በኩል የባለቤትነት ደብተር የሚሰጣቸው መሆኑን የተገለፀልን ሲሆን ሌሎቹ እንደሌላቸው ለማወቅ ተችሏል::

## 5. ስለመሣሪያዎቹ የቴክኒክ ዝርዝርና ዓይነት መረጃዎችን ማሰባሰብ

መሣሪያዎችን የሚያስመጡት ያዶት ኢንጂነሪንግና ሀግቤስ እንዲሁም መሣሪያዎቹን የሚጠቀሙባቸው ባወር ሜድሮክ፣ የመሠረትና የወሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ድርጅትና ኢትዮ ውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ድርጅቶች ስለመሣሪያዎቹ ያሏቸውን የቴክኒክ ዝርዝር (Specification) የሳኩልን ሲሆን በድርጅቶቹ በመገኘት መሣሪያዎችን ለመመልከትና አጠቃላይ ግንዛቤ ለማግኘት ተችሏል::

## 6. የብቃት ምርመራ አገልግሎት ክፍያ፣

በኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ቁጥጥር ምዝገባና የባለቤትነት ደብተር አሰጣጥ መመሪያ ላይ የተመለከተው የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች የቴክኒክ ብቃት ምርመራ አገልግሎት ክፍያ መመሪያው ሲወጣ በወቅቱ የነበረውን የመሣሪያዎች የኪራይ ዋጋ፣ ለዋስትና መያዣነት ያሳቸው ጠቀሜታና የገበያ ተፈሳጊነትን መሠረት ያደረገና አገልግሎቱን ለመስጠት የሚኖረውን ወጪ ለመሸፈን ታቅዶ የወጣ ነበር:: ይህም በሥራ ሂደት ሲታይ ለአገልግሎቱ ከሚኖረው ወጪ ጋር ተመጣጣኝ ሆኖ አግኝተነዋል::

በዚህም መሠረት በመመሪያው ያልተካተቱና አገለግሎቱን በመፈለግ ጥያቄ የቀረበባቸውን መሣሪያዎች ለመመዝገብ የቴክኒክ ብቃት ምረመራ አገልግሎተ ክፍያ ተመን ማውጣቱ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል:: ስለዚህ የአገልግሎት ክፍያ ተመኑን ለማውጣት ቀደም ሲል የወጣውን ቀመር መሠረት በማድረግና መመሪያው ሲወጣና አሁን ያለው የኪራይ ተመን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የመሣሪያዎችን የቀን የኪራይ ተመን በግማሽ በመውሰድ ከዚህ በታች በተመለከተው ሠንጠረዥመሠረት የመሣሪያዎቹ የብቃት ምርመራ አገልግሎት ክፍያ እንዲከፈል አስተያየት ቀርቧል::

# የቴክኒክ ብቃት ምርመራ የአገልግሎት ክፍያ

በየሁለት ዓመት

| ተ.ቁ | የመሣሪያው ዓይነት | የመሣሪያው ብቃት/አቅም (Capacity) | የአገልግሎት ክፍያ በብር |
|---|---|---|---|
| 1 | ፐርከሽን ኬብል ቱል (Percussion Cable Tool rig | ≤ 100 ሜትር | 900 |
| 2 | ፐርከሽን ኬብል ቱል Percussion Cable Tool r/y rig | >100 ሜትር | 950 |
| 3 | ሮተሪ ተብሎ መቆፈሪያ (Rotary or Top headrly r/y rig | ≤ 7 ቶን ሜትር | 1000 |
| 4 | ሮተሪ ተብሎ መቆፈሪያ Rotary or Top headrly r/y rig | > 7 ቶን ሜትር | 1350 |
| 5 | ዋገን ድሪል Wagon dril | ≤ 100 ሚ.ሜ | 300 |
| 6 | ዋገን ድሪል Wagon dril | > 100 ሚ.ሜ | 600 |
| 7 | ቺፕ ስፕሪደር /ጠጠር መበተኛ/ Chip Spreader | ≤ 5 ሜትር | 500 |
| 8 | ቺፕ ስፕሪደር /ጠጠር መበተኛ/ Chip Spreader | > 5 ሜትር | 700 |

ማስታወሻ

የደብተር፣ የሠሌዳ የዕድሣት /ቦሎ/ አገልግሎት ክፍያዎች ቀደም ሲል በወጣው መመሪያ በተመለከተው መሠረት ይሆናል።

አባሪ 5

## የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች የሰሌዳ ኮድ አፃፃፍ

| ተ.ቁ. | የመሣሪያው ዓይነት | የፊደል ኮድ |
|---|---|---|
| 1 | ዶዘር<br>Dozer | DZ |
| 2 | ግሬደር<br>Grader | GR |
| 3 | ሎደር<br>Loader | LD |
| 4 | ኤክስካቫተር<br>Excavator | EX |
| 5 | ስክሬፐር<br>Scraper | SC |
| 6 | ሮለር<br>Roller | RL |
| 7 | ኮምፓክተር<br>Compactor | CM |
| 8 | አስፋልት ማንጠፊያ<br>Asphalt Paver | AP |
| 9 | አስፋልት ማደባለቂያ<br>Asphalt Mixing Plant | AM |
| 10 | ክሬሸር<br>Crusher | CS |
| 11 | ኮንክሪት ባቺንግ ፕላንት<br>Concrete batching Plant | CB |
| 12 | ኮንክሪት ማንጠፊያ<br>Concrete Paver | CP |
| 13 | ክሬን<br>Crane | CR |

ዐደሉ አበባዬ
የመንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር

## 7. የመሣሪያዎች የቴክኒክ ብቃት ምርመራ ስሠራር ዘዴ፣

## መሣሪያዎች የሚሰይበት የሲሪያሉና የሞተር ቁጥር መመዝገብና፣

### 7.1 የመቆፈሪያ መሣሪያዎች የብቃት ምርመራ የአሠራር ዘዴ፣

**መሣሪያው ኬብል ቱል ከሆነ፣ (Cable Tool)**

- የኃይል ማመንጫው መሥራቱን ማረጋገጥ፣
- የመሣሪያው የሥራ አካል አስፈላጊውን እንቅስቃሴ ማለት ወደ ላይና ታች እንዲሁም መዞሩን ማጋገጥ፣
- የተቆፈረውን ማቴሪያል የሚያወጣው መሣሪያ የሚሠራ መሆኑን እንቅስቃሴውን በማየት ማረጋገጥ፣

**መሣሪያው ሮተሪ ቴብል ከሆነ፣ (Rotary Table)**

- የኃይል ማመንጫው መሥራቱን ማረጋገጥ፣
- መድ ፓምፕ (Mud Pump) የሚሠራ መሆኑን በእንቅስቃሴው ማረጋገጥ፣
- የመሣሪያው የሥራ አካል የሆነው ቱል ስትሪንግ አስፈላጊውን እንቅስቃሴ ማለት ወደ ላይና ታች መንቀሣቀሱን ማረጋገጥ፣

**ቶፕ ሄድ ድራይቭ ሪግ ከሆነ፣ (Top Head Drive Rig)**

- የኃይል ማመንጫው መሥራቱን ማረጋገጥ፣
- መድ ፓምፖችና ኮምኘሬሰሮች መሥራታቸውን ማረጋገጥ፣
- የመሣሪያው የሥራ አካል አስፈላጊውን እንቅስቃሴ ማለት መዞሩንና ወደ ላይና ታች መንቀሣቀሱን ማረጋገጥ፣

### 7.2 ዋጎን ድሪል (Wagon-dril)

- ኮምኘሬሰር ያለውና የሚሠራ መሆኑን ማረጋገጥ
- መሣሪያው የሚንቀሳቀስ መሆኑን ማረጋገጥ
- የሥራ አካሉ የሚሠራ መሆኑን በማንቀሳቀስ ማረጋገጥ

### 7.3 የቺፕ ስፕሬደር የብቃት ምርመራ አደራረግ (Chip Spreader)

- የራሱ የኃይል ማመንጫ የሚጠቀም ከሆነ መሥራቱን ማረጋገጥ፣
- ጠጠሩን ለመበተን የሚያገለግለው የሥራ አካል መሥራቱን ማረጋገጥ፣

## Service fee Calculation

| Item No. | Type of Equipment | Capacity | Hourly Rental Rate (RR) Birr/hr | Mrket Available | Collatr Necess | calculated Service fee | Adjusted Service fee | Remark |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | Percussion cab tool rig | ≤ 100 m | 730.73 | 0.4 | 0.8 | 935.33 | 900.00 | |
| 2 | Percussion cab tool rig | > 100 m | 739.47 | 0.4 | 0.8 | 945.92 | 950.00 | |
| 3 | Rotary tab or top head rly rig | ≤ 100Tm | 730.73 | 0.4 | 0.8 | 999.00 | 1000.00 | |
| 4 | Rotary tab or top head rly rig | > 100 Tm | 1063.73 | 0.4 | 0.8 | 1360.92 | 1350.00 | |
| 5 | Wagon drill | ≤ 100mm | 210.13 | 0.4 | 0.8 | 268.96 | 300.00 | |
| 6 | Wagon drill | >100 mm | 452.33 | 0.4 | 0.8 | 578.56 | 600.00 | |
| 7 | Chip Spreader | ≤ 5 m | 233.53 | 0.6 | 0.8 | 448.37 | 450.00 | |
| 8 | Chip Spreader | > 5 m | 309.39 | 0.6 | 0.8 | 594.08 | 600.00 | |

Ser. fee = o.5 RR of one day x MV x CN

Where RR = Rental Rate (see annex 2)

MV = Market availability of the equipment type (see annex 3)

CN = Collateral necessity of the equipment type (see annex 4)

# Equipment Rental Rate

| No | Equipment Type | Rated cap. | HP | Equip. Cost (Birr) | Equip. Life time hour | Equip. life years | salv. val. 10% E (Birr) | Tyre price set Br. | Tyre life Hr. | Dep. cost Br/Hr | Interest Br/Hr | Insurance Rate % | Insurance Cost | Rep. Cost %K | Rep. Cost Br/Hr | Fuel consumption Fuel Fuel L | Fuel consumption Q*D Lt/Hr | Fuel consumption R*Fuel Br/Hr | Service cost Ser. % | Service cost S*T Br/Hr | Tyre cost I/J Br/Hr | Own. Cost K+L+N (Birr/hour) | Oper. Cost P+S+U+V (Birr/hour) | Own+Op. W+X Br/Hr | Ren. Rate Y*1.25 Br/Hr |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| A | B | C | D | E | F | G | H | I | J | K | L | M | N | O | P | Q | R | S | T | U | V | W | X | Y | Z |
| 1 | Percussion cab. Top rig | <100mm | 85 | 3,050,000 | 10,000 | | 305,000 | - | - | 274.5 | 48.57 | 1.2 | 18.3 | 50 | 137.25 | 0.14 | 11.9 | 35.94 | 30 | 10.78 | - | 341.37 | 243.21 | 584.58 | 730.73 |
| 2 | " " | >100m | 150 | 3,600,000 | 10,000 | 5 | 350,000 | - | - | 315 | 68.74 | 1.2 | 21 | 50 | 157.5 | 0.14 | 21 | 63.42 | 30 | 19.03 | - | 391.74 | 204.04 | 595.78 | 739.47 |
| 3 | Rotary stab. Or Top head r/y rig | <7TM | 265 | 3,478,600 | 10,000 | 6 | 347,861 | - | - | 313.07 | 55.4 | 1.2 | 20.87 | 60 | 156.64 | 0.14 | 37.1 | 112.04 | 30 | 33.61 | - | 389.35 | 239.06 | 628.41 | 780.23 |
| 4 | " " | >7TM | 350 | 4,630,800 | 10,000 | 5 | 463,080 | - | - | 416.77 | 76 | 1.2 | 27.78 | 50 | 208.39 | 0.14 | 49 | 147.98 | 30 | 44.39 | - | 520.55 | 323.76 | 844.37 | 1063.73 |
| 5 | Wagon drill | <100mm | 150 | 1,183,838 | 10,000 | 5 | 118,384 | | | 106.55 | 20.1 | 1.2 | 7.10 | 50 | 53.27 | 0.14 | 21 | 63.42 | 14 | 8.88 | - | 133.75 | 85.15 | 218.90 | 210.13 |
| 6 | " " | >100mm | 200 | 2,482,000 | 10,000 | 5 | 248,200 | | | 223.38 | 42.15 | 1.2 | 14.89 | 50 | 111.69 | 0.14 | 28 | 84.56 | 14 | 11.84 | - | 280.42 | 81.44 | 361.86 | 452.33 |
| 7 | Chip spreader | <5m | 116 | 978,196 | 14,000 | 7 | 97,820 | 7200 | 2200 | 68.80 | 17.85 | 1.2 | 5.87 | 80 | 45.28 | 0.14 | 16.24 | 49.04 | 20 | 9.81 | 3.27 | 80.31 | 105.61 | 185.82 | 233.53 |
| 8 | " " | >5m | 170 | 1,254,250 | 15,000 | 7.5 | 125,425 | 7200 | 2200 | 67.73 | 22.92 | 1.2 | 7.53 | 80 | 54.18 | 0.14 | 23.8 | 71.84 | 20 | 14.35 | 3.27 | 98.18 | 149.34 | 247.52 | 309.39 |

ሰንጠረዥ 3

## የመሣሪያዎች የገበያ ተፈላጊነት

| ተ/ቁ | የመሣሪያው ዓይነት | መሳሪያው የሚያገለግልባቸው የስራ ዓይነቶች | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | በህንፃ | በመንገድ | ቁፋሮ | ቤቶች ምርቶች |
| 1 | ሪግ ማሽን | | | ✓ | |
| 2 | ቻን ሰንሪደር | በከፊል | ✓ | | በከፊል |

የመሣሪያው የገበያ ተፈላጊነት በሚሰጣቸው የስራ ዓይነቶች ብዛት መሠረት

ለአንድ ዓይነት አገልግሎት የሚውል = ዝቅተኛ 0.4
ለሁለት " " " = መካከለኛ 0.6
ለሦስት " " " = ከፍተኛ 0.8
ለአራት " " " = በጣም ከፍተኛ 0.9

## የኮንስትራክሽን መሣሪያዎችን መርምሮ ለመመዝገብ የቀረበ የክፍያ ተመን ስሌት ዝርዝር

### የስሌቱ መነሻ

አክ - የመሣሪያው የምዝገባና የእድሳት አገልግሎት ክፍያ

ቀኪ - የመሣሪያው የአንድ ቀን /ስምንት ሰዓት፣ የኪራይ ዋጋ

ገተ - መሣሪያው በገበያ ላይ ያለው የኪራይ ተፈላጊነት

ኮጠ - መሣሪያው ለኮሳተራልና ለመሳሰሉት ያለው ጠቀሜታ

| |
|---|
| ስሌቱ → አክ =(ቀኪ x ገተ x ኮጠ) |

መሣሪያው በገበያ ላይ ያለው የኪራይ ተፈላጊነት / ገተ/

| | |
|---|---|
| ጥሩ | 0.8 - 1.0 |
| መካከለኛ | 0.6 - 0.8 |
| ዝቅተኛ | 0.4 - 0.6 |

ለዋስትና መያዣነት ለመሳሰሉት አገልግሎት ያላቸው ጠቀሜታ /ኮጠ/

| | |
|---|---|
| ጥሩ | 0.8 - 1.0 |
| መካከለኛ | 0.6 - 0.8 |
| ዝቅተኛ | 0.4 - 0.6 |

የመሣሪያ የአገልግሎት ክፍያ ቀመር በየቦታው ተተክለው የሚሠሩና የምርት ውጤታቸውን በማጓጓዝ ጥቅም ላይ የሚውሉ የድንጋይ ወፍጮ፣ የአስፋልት ፕላንትና የኮንክሪት ፕላንቶች መሣሪያዎች በ0.5 እንዲባዛ ያደርጋል።

ጥቅምት 01 ቀን 2003 ዓ/ም

# የ ው ስ ጥ መ ፃ ፃ ፊ ያ

ለ → ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት የሥራ ሂደት

ከ → ምዝገባ ቡድን ተመስገን ተስፋዬ ገ/ፃዲቅ
የምዝገባ ቡድን ዳይሬክተር

ጉዳዩ → አዲስ የኮን/መሣ/ለመመዝገብ መመሪያ ስለመጠየቅ፣

ከጊዜ ወደ ጊዜ ለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ አስፈላጊ የሆኑና ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን የያዙ የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ወደ ሀገሪቱ በመግባት ላይ ስለመሆናቸው ባለጉዳዮች ከሚያቀርቧቸው የአገልግሎት ጥያቄ መረዳት ይቻላል።

ከነዚህም አንዱ ኬ.ኬ. ኃ.የተ./የግ/ኩባንያ ተጎታች የኮንክሪት ፓምፕ (trailer-mounted concrete pumps) እንዲመዘገብለት በቁጥር ኬ.ኬ.125/03 በ20/01/03 በፃፈው ማመልከቻ ጠይቆናል።

ሆኖም ደንበኛው ያቀረበው የመሣሪያ ዓይነት በመመሪያችን ውስጥ ከተዘረዘሩት ውጪ ነው።

ስለሆነም መሣሪያው ለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ጠቃሚታው የጎላ በመሆኑ በቡድኑ እንዲመዘገብ መመሪያ ይሰጥ ዘንድ ይህን የውሣኔ ሀሣብ እናቀርባለን። በተጨማሪም የአገልግሎት ክፍያው ከፍ ባለ እርከን ከሚገኘው ከኮንክሪት ባችንግ ፕላንት ጋር አንድ አይነት እንዲሆን ማለትም፣

| | |
|---|---|
| ከ80 ቶን በሰዓት በታች | ብር 1500.00 /አንድ ሺህ አምስት መቶ/ |
| ከ80-150 ቶን በሰዓት | ብር 3000.00/ሦስት ሺህ አምስት መቶ/ |
| ከ150 ቶን በሰዓት በላይ | ብር 3500.00 / ሦስት ሺህ አምስት መቶ/ |

እንዲሆን እናቀርባለን።

ከሰላምታ ጋር

ሐምሌ 16 ቀን 1996 ዓ.ም.

# የ ው ስ ጥ   መ ል እ ክ ት

ለ ⇨ ለቡር የኮንስትራክሽንና ፐብሊክ ዩትሊትስ ማኔጅመንት
ዘርፍ ሚ/ር ዴኤታ

ከ ⇨ ከዲዛይንና ኮንስትራክሽን ቁጥጥር ጽ/ቤት

ጉዳዩ ⇨ <u>ተጨማሪ የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ምዝገባና ድጋሚ</u>
<u>ምርመራ ለማድረግ የቀረበ መመሪያ እንዲፀድቅልን ስለመጠየቅ፤</u>

በመ/ቤታችን የሚመዘገቡ የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ለመዘጋገብ ሚያዝያ 1993 በወጣው መመሪያ መሠረት መሆኑ ይታወቃል:: በዚህ መመሪያ ያልተካተቱ የግንባታ መሣሪያዎች በአገልግሎት ፈላጊዎች በቀረበው ጥያቄ መሠረት ለመመዝገብ አሠራሩ መመሪያን የተከተለ እንዲሆን የቀረበውን ረቂቅ ጥናት እንዲሠራበት እንዲ ፀድቅልን በትህትና እንጠይቃለን::

ከማክበር ከሠላምታ ጋር

(1) [illegible]

(2) [illegible]

አባሪ፡ 1 ጥራዝ

በመሠረተ ልማት ሚኒስቴር
የዲዛይን ኮንስትራክሽን ቁጥጥር ጽ/ቤት

# ለምዝገባ ስለሚቀርቡ ተጨማሪ የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች የቀረበ ረቂቅ ጥናት

ሐምሌ 1996 ዓ.ም.

# ማውጫ


መግቢያ ........................................................................ 1

1 የጥናቱ ዓላማ........................................................................ 2

2 የጥናቱ አጠናን ዘዴ ........................................................................ 2

3 በጥናቱ እንዲካተቱ የተደረጉ መሣሪያዎች........................................ 2

4 ስለመሣሪያዎች አመዘጋገብ የተደረገ ማጣራት........................................ 2

5 ስለመሣሪያዎች የቴክኒክ ዝርዝርና ዓይነት መረጃዎችን ማሰባሰብ........ 3

6 የብቃት ምርመራ አገልግሎት ክፍያ........................................ 3

7 የመሣሪያዎች የቴክኒክ ብቃት ምርመራ አሠራር ዘዴ........................ 5

8 አባሪዎች፣

1 የአገልግሎት ክፍያ ስሌት

2 የመሣሪያ የኪራይ ተመን ስሌት

3 የመሣሪያዎች የገበያ ተፈላጊነት ነጥብ ሰ[illegible]

4 የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች የአገልግሎት ክፍያ ለመ[illegible]ወጣ ቀመር

# መግቢያ

መንግሥት የግል ዘርፉን ለማበረታታት ካወጣቸው አዋጆች ውስጥ የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ምዝገባና ቁጥጥር አዋጅ 177/91 የሚጠቀስ ነው:: በዚህ አዋጅ መሠረት የኮንስትራክሽን መሣሪያ ባለንብረቶች መሣሪያዎቻቸውን በማስመዝገብ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ለመውሰድ ለዋስትናና መያዣነት አገልግሎት እየተጠቀሙበት ይገኛሉ::

የአዋጁ ተጠቃሚ የሆኑት አዋጁን ተከትሎ በወጣው መመሪያ ውስጥ ዝርዝራቸው የተካተቱት የኮንስትራክሽን መሣሪያ ባለንብረቶች ሲሆኑ ከዚህ ውጭ የሆኑ መሣሪያ ያሏቸው ባለንብረቶች የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ለመሆን ጥያቄ በማቅረብ ላይ ናቸው:: በዚህም መሠረት የባለንብረቶችን ጥያቄ መነሻ በማድረግ በዚህ ጥናት ውስጥ የተካተቱት የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች መመዝገብ እንዲችሉ ለማድረግ ይህ ጥናት ቀርቧል::

1. <u>የጥናቱ ዓላማ፣</u>

የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች የባለቤትነት መታወቂያ ደብተርና ሠሌዳ አሠጣጥ በሚ/ር መ/ቤቱ የወጣውን መመሪያ ተከትሎ የሚከናወን ስለሆነ በዚህ ጥናት የተካተቱት የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ዝርዝር የመመሪያው አካል እንዲሆኑ ለማድረግና አፈጻጸሙ ሥርዓት የተከተለ እንዲሆን ለማድረግ ነው፡፡

2. <u>የጥናቱ አጠናን ዘዴ፣</u>

- በአገልግሎቱ ፈላጊዎች የቀረቡትን ጥያቄዎች መነሻ በማድረግ በጥናቱ መካተት ያለባቸው መሣሪያዎች መለየት፣
- በጥናቱ የተካተቱ መሣሪያዎች በሌሎች የመንግሥት አካላት የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ይሰጣቸው እንደሆነ ማጣራት፣
- ስለመሣሪያዎቹ አይነትና የቴክኒክ ዝርዝር መረጃዎችን በመሰብሰብና መሣሪያዎቹን በማየት አጠቃላይ ግንዛቤ መውሰድ፣
- በመሣሪያዎች የቴክኒክ ብቃት ምርመራ አደራረግ ወቅት የሚኖሩ የአገልግሎት ክፍያዎችን ቀደም ሲል በወጣው መመሪያ መሠረት መተመን፣

3. <u>በጥናቱ እንዲካተቱ የተደረጉ መሣሪያዎች፣</u>

ከአገልግሎት ፈላጊዎች በቀረበው ጥያቄ መሠረት የመቆፈሪያና(**Drilling Rigs**) የጠጠር መበተኛ (**Chip Spreader**) መሣሪያዎች በጥናቱ ተካተዋል፡፡

4. <u>ስለ መሣሪያዎቹ ለመዘገብ የተደረገ ማጣራት፣</u>

የጉድጓድ መቆፈሪያ መሣሪያ ባለንብረቶች የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ይሰጣቸው እንደሆነ ለማወቅ በተደረገ ማጣራት ተጠይቀው በተሽከርካሪዎች ላይ ተገጥመው ለሚሰሩት በመንገድ ትራንስፖርት ባለሥልጣን በኩል የባለቤትነት ደብተር የሚሰጣቸው መሆኑን የተገለፀልን ሲሆን ሌሎቹ እንደሌላቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡

## 5. ስለመሣሪያዎች የቴክኒክ ዝርዝርና ዓይነት መረጃዎችን ማሰባሰብ

መሣሪያዎችን የሚያስመጡት ያዶት ኢንጂነሪንግና ሀግቤስ እንዲሁም መሣሪያዎቹን የሚጠቀሙባቸው ባወር ሜድርከ፣ የመሠረትና የወሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ድርጅትና ኢትዮ ውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ድርጅቶች፣ ስለመሣሪያዎቹ ያሏቸውን የቴክኒክ ዝርዝር (Specification) የላኩልን ሲሆን በድርጅቶቹ በመገኘት መሣሪያዎችን ለመመልከትና አጠቃላይ ግንዛቤ ለማግኘት ተችሏል።

## 6. የብቃት ምርመራ አገልግሎት ክፍያ፣

በኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ቁጥጥር ምዝገባና የባለቤትነት ደብተር አሰጣጥ መመሪያ ላይ የተመለከተው የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች የቴክኒክ ብቃት ምርመራ አገልግሎት ክፍያ መመሪያው ሲወጣ በወቅቱ የነበረውን የመሣሪያዎች የኪራይ ዋጋ፣ ለዋስትና መያዣነት ያላቸው ጠቀሜታና የገበያ ተፈላጊነትን መሠረት ያደረገና አገልግሎቱን ለመስጠት የሚኖረውን ወጪ ለመሸፈን ታቅዶ የወጣ ነበር። ይህም በሥራ ሂደት ሲታይ ለአገልግሎቱ ከሚኖረው ወጪ ጋር ተመጣጣኝ ሆኖ አግኝተነዋል።

በዚህም መሠረት በመመሪያው ያልተካተቱና አገልግሎቱን በመፈለግ ጥያቄ የቀረበባቸውን መሣሪያዎች ለመመዝገብ የቴክኒክ ብቃት ምርመራ አገልግሎተ ክፍያ ተመን ማውጣቱ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። ስለዚህ የአገልግሎት ክፍያ ተመኑን ለማውጣት ቀደም ሲል የወጣውን ቀመር መሠረት በማድረግና መመሪያው ሲወጣና አሁን ያለው የኪራይ ተመን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የመሣሪያዎችን የቀን የኪራይ ተመን በግማሽ በመውሰድ ከዚህ በታች በተመለከተው ሠንጠረዥ መሠረት የመሣሪያዎቹ የብቃት ምርመራ አገልግሎት ክፍያ እንዲከፈል አስተያየት ቀርቧል።

## የቴክኒክ ብቃት ምርመራ የአገልግሎት ክፍያ

በየሁለት ዓመት

| ተ.ቀ | የመሣሪያው ዓይነት | የመሣሪያው አቅም (Capacity) | የአገልግሎት ክፍያ በብር |
|---|---|---|---|
| 1 | ፐርከሽን ኬብል ቱል (Percussion Cable Tool rig | ≤ 100 ሜትር | 900 |
| 2 | ፐርከሽን ኬብል ቱል Percussion Cable Tool r/y rig | >100 ሜትር | 950 |
| 3 | ሮተሪ ተብለ መቆፈሪያ (Rotary or Top headrly r/y rig | ≤ 7 ቶን ሜትር | 1000 |
| 4 | ሮተሪ ተብለ መቆፈሪያ Rotary or Top headrly r/y rig | > 7 ቶን ሜትር | 1350 |
| 5 | ዋገን ድሪል Wagon dril | ≤ 100 ሚ.ሚ | 300 |
| 6 | ዋገን ድሪል Wagon dril | > 100 ሚ.ሚ | 600 |
| 7 | ቺፕ ስፕሬደር /ጠጠር መበተኛ/ Chip Spreader | ≤ 5 ሜትር | 500 |
| 8 | ቺፕ ስፕሬደር /ጠጠር መበተኛ/ Chip Spreader | > 5 ሜትር | 700 |

ማስታወሻ

የደብተር፣ የሠሌዳና የዕድሣት /ቦሎ/ አገልግሎት ክፍያዎች ቀደም ሲል በወጣው መመሪያ በተመለከተው መሠረት ይሆናል።

WD

CH

Drilint Rig = DR

መሣሪያዎች የቴክኒክ ብቃት ምርመራ አሠራር ዘዴ፣

መሣሪያዎች የሚለዩበት የሲሪያልና የሞተር ቁጥር መመዝገብና፣

7.1 የመቆፈሪያ መሣሪያዎች የብቃት ምርመራ የአሠራር ዘዴ፣

**መሣሪያው ኬብል ቱል ከሆነ፣ ( Cable Tool)**

- የኃይል ማመንጫው መሥራቱን ማረጋገጥ፣
- የመሣሪያው የሥራ አካል አስፈላጊውን እንቅስቃሴ ማስት ወደ ላይና ታች እንዲሁም መዞሩን ማጋገጥ፣
- የተቆፈረውን ማቴሪያል የሚያወጣው መሣሪያ የሚሠራ መሆኑን እንቅስቃሴውን በማየት ማረጋገጥ፣

**መሣሪያው ሮተሪ ቴብል ከሆነ፣ ( Rotary Table)**

- የኃይል ማመንጫው መሥራቱን ማረጋገጥ፣
- መድ ፓምፑ **(Mud Pump)** የሚሠራ መሆኑን በእንቅስቃሴው ማረጋገጥ፣
- የመሣሪያው የሥራ አካል የሆነው ቱል ስትሪንግ አስፈላጊውን እንቅስቃሴ ማስት ወደ ላይና ታች መንቀሣቀሱን ማረጋገጥ፣

**ትፕ ሄድ ድራይቭ ሪግ ከሆነ፣ (Top Head Drive Rig)**

- የኃይል ማመንጫው መሥራቱን ማረጋገጥ፣
- መድ ፓምፖችና ኮምኘሬሰሮች መሥራታቸውን ማረጋገጥ፣
- የመሣሪያው የሥራ አካል አስፈላጊውን እንቅስቃሴ ማስት መዞሩንና ወደ ላይና ታች መንቀሣቀሱን ማረጋገጥ፣

7.2 **ዋገን ድሪል (Wagon dril)**

- ኮምኘሬሰር ያለውና የሚሠራ መሆኑን ማረጋገጥ
- መሣሪያው የሚንቀሳቀስ መሆኑን ማረጋገጥ
- የሥራ አካሉ የሚሠራ መሆኑን በማንቀሳቀስ ማረጋገጥ

7.3 **የቺፕ ስኘሬደር የብቃት ምርመራ አደራረግ (Chip Spreader)**

- የራሱ የኃይል ማመንጫ የሚጠቀም ከሆነ መሥራቱን ማረጋገጥ፣
- ጠጠሩን ለመበተን የሚያገለግለው የሥራ አካል መሥራቱን ማረጋገጥ፣

## Service fee Calculation

| Item No. | Type of Equipment | Capacity | Hourly Rental Rate (RR) Birr/hr | Mrket Available | Collatr Necess | calculated Service fee | Adjusted Service fee | Remark |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | Percussion cab tool rig | ≤ 100 m | 730.73 | 0.4 | 0.8 | 935.33 | 900.00 | |
| 2 | Percussion cab tool rig | > 100 m | 739.47 | 0.4 | 0.8 | 945.92 | 950.00 | |
| 3 | Rotary tab or top head rly rig | ≤ 100Tm | 730.73 | 0.4 | 0.8 | 999.00 | 1000.00 | |
| 4 | Rotary tab or top head rly rig | > 100 Tm | 1063.73 | 0.4 | 0.8 | 1360.92 | 1350.00 | |
| 5 | Wagon drill | ≤ 100mm | 210.13 | 0.4 | 0.8 | 268.96 | 300.00 | |
| 6 | Wagon drill | >100 mm | 452.33 | 0.4 | 0.8 | 578.56 | 600.00 | |
| 7 | Chip Spreader | ≤ 5 m | 233.53 | 0.6 | 0.8 | 448.37 | 450.00 | |
| 8 | Chip Spreader | > 5 m | 309.39 | 0.6 | 0.8 | 594.08 | 600.00 | |

Ser. fee = o.5 RR of one day x MV x CN

Where RR = Rental Rate (see annex 2)

MV = Market availability of the equipment type (see annex 3)

CN = Collateral necessity of the equipment type (see annex 4)

# Equipment Rental Rate

| No | Equipment Type | Rated cap. | HP | Equip. Cost (Birr) | Eqip. Life time hour | Equp. life years | salv. val. 10%E (Birr) | Tyre price set Br. | Tyre life Hr. | Dep. cost Br/Hr | Interest Br/Hr | Insurance Rate % | Insurance Cost | Rep. Cost %K | Rep. Cost Br/Hr | Fuel consumption fuel fact. | Fuel consumption Q*D L/Hr | Fuel consumption R*Fcost Br/Hr | Service cost Sfac. % | Service cost S*T Br/Hr | Tyre cost I/J Br/Hr | Own. Cost K+L+N (Birr/hour) | Oper. Cost P+S+U+V (Birr/hour) | Ow+Op W+X Br/Hr | Ren. Rate Y*1.25 Br/Hr |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| A | B | C | D | [illegible] | F | G | H | I | J | K | L | M | N | O | P | Q | R | S | T | U | V | W | X | Y | Z |
| | Percussion cab. Top rig | <100mm | 85 | 3,050,000 | 10,000 | | 305,000 | - | - | 274.5 | 48.57 | 1.2 | 18.3 | 50 | 137.25 | 0.14 | 11.9 | 35.94 | 30 | 10.78 | - | 341.37 | 243.21 | 584.58 | 730.73 |
| | | >100m | 150 | 3,500,000 | 10,000 | 5 | 350,000 | - | - | 315 | 55.74 | 1.2 | 21 | 50 | 157.5 | 0.14 | 21 | 63.42 | 30 | 19.03 | - | 391.74 | 204.04 | 595.78 | 739.47 |
| | Rotary cab. Or Top head | <7TM | 265 | 3,478,605 | 10,000 | 5 | 347,861 | - | - | 313.07 | 55.4 | 1.2 | 20.87 | 50 | 156.54 | 0.14 | 37.1 | 112.04 | 30 | 33.61 | - | 389.35 | 239.09 | 628.44 | 780.2 |
| | | >7TM | 350 | 4,630,802 | 10,000 | 5 | 463,080 | - | - | 416.77 | 76 | 1.2 | 27.78 | 50 | 208.39 | 0.14 | 49 | 147.98 | 30 | 44.39 | - | 520.56 | 323.76 | 844.32 | 1063.7 |
| | Wagon drill | <100mm | 150 | 1,183,838 | 10,000 | 5 | 118,384 | | | 106.55 | 20.1 | 1.2 | 7.10 | 50 | 53.27 | 0.14 | 21 | 63.42 | 14 | 8.88 | - | 133.75 | 86.15 | 219.90 | 210.1 |
| | | >100mm | 200 | 2,482,000 | 10,000 | 5 | 248,200 | | | 223.38 | 42.15 | 1.2 | 14.89 | 50 | 111.69 | 0.14 | 28 | 84.56 | 14 | 11.84 | - | 280.42 | 81.44 | 361.86 | 452.33 |
| | Chip spreader | <5m | 116 | 978,196 | 14,000 | 7 | 97,820 | 7200 | 2200 | 56.60 | 17.85 | 1.2 | 5.87 | 80 | 45.28 | 0.14 | 16.24 | 49.04 | 20 | 9.81 | 3.27 | 80.31 | 106.51 | 186.82 | 233.5 |
| | | >5m | 170 | 1,254,250 | 15,000 | 7.5 | 125,425 | 7200 | 2200 | 67.73 | 22.92 | 1.2 | 7.53 | 80 | 54.18 | 0.14 | 23.8 | 71.88 | 20 | 14.38 | 3.27 | 98.18 | 149.34 | 247.52 | 309.39 |

# የመሣሪያዎች የገበያ ተፈላጊነት

| ተ/ቁ | የመሣሪያው ዓይነት | መሳሪያው የሚያገለግልባቸው የስራ ዓይነቶች | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ለህንፃ | ለመንገድ | ቁፋሮ | ሌሎች ሥራዎች |
| 1 | ሪግ ማሽን | | | ✓ | |
| 2 | ቺፕ ስፕሬደር | በከፊል | ✓ | | በከፊል |

የመሣሪያው የገበያ ተፈላጊነት በሚሰጣቸው የስራ ዓይነቶች ብዛት መሠረት

ለአንድ ዓይነት አገልግሎት የሚውል = ዝቅተኛ 0.4
ለሁለት " " " = መካከለኛ 0.6
ለሦስት " " " = ከፍተኛ 0.8
ለአራት " " " = በጣም ከፍተኛ 0.9

የኮንስትራክሽን መሣሪያዎችን መርምሮ ለመመዝገብ የቀረበ
የክፍያ ተመን ስሌት ዝርዝር

የስሌቱ መነሻ

አክ - የመሣሪያው የምዝገባና የእድሳት አገልግሎት ክፍያ
ቀኪ - የመሣሪያው የአንድ ቀን /ስምንት ሰዓት፣ የኪራይ ዋጋ
ገተ - መሣሪያው በገበያ ላይ ያለው የኪራይ ተፈላጊነት
ኮጠ - መሣሪያው ለኮላተራልና ለመሳሰሉት ያለው ጠቀሜታ

ስሌቱ → አክ =(ቀኪ x ገተ x ኮጠ)

መሣሪያው በገበያ ላይ ያለው የኪራይ ተፈላጊነት / ገተ./

| | |
|---|---|
| ጥሩ | 0.8 - 1.0 |
| መካከለኛ | 0.6 - 0.8 |
| ዝቅተኛ | 0.4 - 0.6 |

ለዋስትና መያዣነት ለመሳሰሉት አገልግሎት ያላቸው ጠቀሜታ /ኮጠ/

| | |
|---|---|
| ጥሩ | 0.8 - 1.0 |
| መካከለኛ | 0.6 - 0.8 |
| ዝቅተኛ | 0.4 - 0.6 |

የመሣሪያ የአገልግሎት ክፍያ ቀመር በየቦታው ተተክለው የሚሠሩና የምርት ውጤታቸውን በማጓጓዝ ጥቅም ላይ የሚውሉ የድንጋይ ወፍጮ፣ የአስፋልት ፕላንትና የኮንክሪት ፕላንቶች መሣሪያዎች በ0.5 እንዲባዛ ያደርጋል።

# የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ቁጥጥር ምዝገባና የባለቤትነት ደብተር አሰጣጥ መመሪያ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር

The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Works and Urban Development

ቁጥር H1-885/መ240/74
No.

አባሪ ..........
Encl.

አዲስ አበባ 04 ነሐሴ 1993 ቀን ፲፱፻ .......... ዓ.ም.
Addis Ababa .......... Date 19 ..........

የፖ.ሣ.ቁ. / P.O.Box 5608
የስልክ ቁ. / Tel. No. 51 00 00

ለኮን/መሣሪያ ምዝገባ፣ ጥናትና
የቴክኒክ ቁጥጥር መምሪያ
ሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር

የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ቁጥጥር ምዝገባና የባለቤትነት ደብተር አሰጣጥ መመሪያ በቁጥር ዘ1-885/መ-240/43 ሚያዝያ 30 ቀን 1993 በተፃፈ መሸኛ ደብደቤ ጽድቆ የተላከላችሁና ሥራውም መጀመሩ ይታወቃል።

ሆኖም በሥራ ሂደት በመመሪያው ያልተካተቱትን የኮንስትራክሽን መሣሪያ ባለንብረት ማስረጃዎች ለማስተናገድ እንዲቻል፣

1. የመንግሥት መ/ቤቶችና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ሆነው ዲክላራሲዮንና የፍ/ቤት ማስረጃ ማቅረብ የማይችሉ ከሆነ ንብረቱ የራሳቸው ስለመሆኑና የመሣሪያውን ባለንብረትነት አስመልክቶ ጠያቂ አካል ቢመጣ በህግ ተጠያቂ ስለመሆናቸው የሚያረጋግጥ በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ የተፈረመ ደብደቤ እንዲያቀርቡ ተደርጉ የባለቤተነት ደብተር እንዲሰጣቸው፣

2. ከመንግሥት መ/ቤቶችና ከመንግሥት የልማት ድርጅቶች በጨረታ ለተለያዩ ገገርዎች የተሸጡ መሣሪያዎች ሆነው ዲክላራሲዮን ወይም የፍ/ቤት ማስረጃ ሊቀርብላቸው የማይችሉትን በሻጭ መ/ቤቶች በበላይ ኃላፊ የሚሰጠውን ደብዳቤ መሠረት በማድረግ የባለቤትነት ደብተር እንዲሰጣቸው፣

3. ከኮንስትራክሽን መሣሪያ አስመጪዎች የተገዙ ከሆኑ ባለንብረቶች አስመጪዎቹ ጋ ያለውን የኦርጂናል ዲክላራሲዮን ፎቶ ኮፒውንና የአስመጪውን ድርጅት ማህተም አስደርገው ካቀረቡ የባለቤትነት ደብተር እንዲሰጣቸው፣

4. የፍ/ቤት ማስረጃ፣ ዲክላራሲዮንና ከላይ በተራ ቁጥር 1፣ 2 እና 3 ውስጥ ሊካተቱ የማይችሉ ማስረጃዎች ያሏቸው የኮንስትራክሽን መሣሪያ ባለንብረቶች ንብረቱ የራሳቸው መሆኑን በመግለጽ ተቃዋሚ መኖር አለመኖሩን በጋዜጣ እንዲያሳውጁ ተደርጉ የባለቤትነት ደብተር እንዲሰጣቸው እንዲደረግ፣

ኃይሉ አበጋዙ
የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስትር

ከተራ ቁጥር 1-4 የተዘረዘሩትም የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ቁጥጥር ምዝገባና [illegible] ደብተር አሰጣጥ መመሪያ አካል ሆነው እንዲሰራባቸው አስታውቃ ለሁ።

ከሰላምታ ጋር

ኃይሉ አሰግዴ
የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስትር

ግልባጭ፣

- ለም/ሚኒስትር ጽ/ቤት
- ለዋና መሐንዲስ ጽ/ቤት
- ለሕግ አገልግሎት
  ሥራና ከተማ ልማት ሚ/ር

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር

The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Works and Urban Development

1993

አዲስ አበባ ________ ቀን 19______ ዓ.ም.
Addis Ababa ________ Date 19 ________

የፖ.ሣ.ቁ. / P.O.Box 5608

የስልክ ቁ. / Tel.No. 51 00 00

ለኮንስትራክሽን መሣ/ምዝገባ፣ ጥናትና የቴክኒክ ቁጥጥር መምሪያ
<u>ሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር</u>

በዚህ ደብዳቤ ሸኚነት 1 ጥራዝ የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ቁጥጥር ምዝገባና የባለቤትነት ደብተር አሰጣጥ መመሪያ ጸድቆ የተላከላችሁ ስለሆነ በመመሪያው መሠረት እንድትሠሩ አስታውቃለሁ።

ከሰላምታ ጋር

ኃይሌ አሰግዴ
የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስትር

## ማውጫ


| | | |
|---|---|---|
| 1 | አውጪው ባለሥልጣን | 1 |
| 2 | አጭር ርዕስ | 1 |
| 3 | ስለ ኮንስትራክሽን መሣሪያዎች አመዘጋገብና የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር አሰጣጥ | 1 |
| 4 | ስለ መለያ ቁጥር አሰጣጥ | 3 |
| 5 | ስለ ኮንስትራክሽን መሣሪያዎች የባለይዞታ ስምና የመለያ ቁጥር ማዛወር | 3 |
| 6 | ለጠፋ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ወይም የመሣሪያ መለያ ቁጥር ምትክ አሰጣጥ | 5 |
| 7 | የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ለብቃት ምርመራ መቅረብ | 5 |
| 8 | በእድሣት ጊዜ የሚደረግ ምርመራ | 6 |
| 9 | የእድሣት ጊዜ ስለመወሰን | 6 |
| 10 | የምዝገባና የእድሣት ቦታ ስለመወሰን | 6 |
| 11 | የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ምዝገባና እድሣት የአገልግሎት ክፍያ | 7 |
| 12 | የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች የብቃት ምርመራ አሠራርና የቀጠና አከላለል | 10 |
| 13 | የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች የቴክኒክ ደህንነት ምርመራ አሠራር ዘዴ | 12 |

አባሪዎች፣

አባሪ 1 - የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ምዝገባ መማልከቻ ቅጽ

አባሪ 2 - የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች የምርመራ ቅጽ

አባሪ 3 - የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር

አባሪ 4 - የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ሰሌዳ

አባሪ 5 - የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች የሰሌዳ ኮድ አጻጻፍ


ኃይሌ አሰግዴ

የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስትር

# የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ቁጥጥር ምዝገባና
# የባለቤትነት ደብተር አሠጣጥ መመሪያ

## 1. አውጪው ባለሥልጣን፣

የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ስለኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ምዝገባና ቁጥጥር በወጣው አዋጅ ቁ. 177/1991 አንቀጽ 5/2 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል::

## 2. አጭር ርዕስ፣

ይህ መመሪያ የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ቁጥጥር፣ ምዝገባና የባለቤትነት ደብተር አሰጣጥ መመሪያ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

## 3. ስለኮንስትራክሽን መሣሪያዎች አመዘጋገብና የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር አሰጣጥ፣

3.1 በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመዘገቡና የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር የሚሰጣቸው የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች የሚከተሉት ናቸው::

ሀ. በጐማ ወይም በብረት ስንሰለት የሚንቀሳቀሱ እንደ ዶዘር፣ ኤክስካቫተር፣ ግሬደር፣ ሎደር፣ ኮምፓክተር፣ አስፋልት ማንጠፊያ፣ ኮንክሪት ማንጠፊያ፣ ስክሬፐር፣ ሮለር፣

ለ. ከቦታ ቦታ እየተወሰዱ ተተክለው የሚሠሩ እንደ ኮንክሪት ባቺንግ ፕላንት፣ አስፋልት ማክሲንግ ፕላንት፣ ክሬሸር፣ ክሬን፣

3.2 የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ስለማስፈለጉ፣

3.2.1 የሀገሪቱን የኮንስትራክሽን አቅም ትክክለኛ ገጽታ ለማወቅና የሚታቀዱት የልማት ዕቅዶች በተገቢው መንገድ ለመምራት በአገሪቱ በመንግሥትና በግል የተያዙትን የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ብዛት በዓይነት መዝግቦ መያዝ አስፈላጊ በመሆኑ፣

3.2.2 የሥራ ፈቃድ ያወጡትንና የሚያወጡትን የሥራ ተቋራጮች የመሣሪያ አቅም ለመገምገምና ባለቤትነታቸው ትክክለኛ መሆኑን ለማረጋገጥ ለሚደረገው ክትትል እገዛ ለማድረግ፣

3.2.3 የመሣሪያ አከራዮችን ለመመዝገብና ለመቆጣጠር፣

3.2.4 ወደ አገር ውስጥ የሚገቡና ከአገር የሚወጡ የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ከሚኒስቴሩ መ/ቤት የማስገቢያና የማውጫ ፈቃድ ማግኘታቸውን ለመቆጣጠር ሲባል ነው::

3.3 የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ለማግኘት የሚቀርቡ ሰነዶች፣

ኃይሌ አሰግዴ
የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስትር